SmaRT Ethiopia

INITIATIVE ON Sustainable Animal Productivity

CGIAR


Photo ILRI/Zerihun Sewunet

# በኢትዮጵያ የእንስሳት ገበያዎች ዉስጥ ያሉ አገልግሎቶች ፍላጎት እና ፋይዳ

*በግርማ ተስፋሁን ካሴ፣ ፍሬሰንበት ዘለቀ፣ ወይንሸት አስናቀ፣ አይናለም ሀይሌና ባርባራ ሪሸኮዊስኪ*

## ቁልፍ መልዕክቶች

- የገበያ መገልገያዎች እጥረት እና ከፍተኛ የግብይት ወጭ መገለጫዎቹ የሆነው ዘልማዳዊው የእንስሳት ግብይት ሥርዓት በግብርናው ዘርፍ ውስጥ በማምረት እና በፍጆታ ዙሪያ ያሉ ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል አይደለም፡፡
- በቂ ያልሆኑ የገበያ መሠረተ ልማቶች የንግድ እና የግብይት ሥራ ለማከናወን እንቅፋት ይፈጥራሉ፡፡ ይህም የአርሶ አደሮችን የንግድ እና ግብይት ወጪዎችን በማናር ከገበያው ተሳትፎ የሚያገኙት ጥቅም ውስን እንዲሆን ያደርገዋል፡፡
- በኢትዮጵያ ውስጥ አርሶ አደሮች ከእንስሳት እርባታ የሚያገኙት ጥቅም በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ሳይንሳዊ የሆኑ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የግብይት ሥርዓትን በማሻሻል ከእንስሳት እርባታ የሚገኘዉን ጥቅም ማሳደግ ይቻላል፡፡ የእንስሳት ግብይት መሠረተ ልማቶችን ማሻሻል ይህንን አላማ ለማሳካት ሊከናወኑ ከሚገባቸው ተግባራት አንዱ ነው፡፡
- በግብርናና ገጠር ልማት ዙሪያ ያሉ ፖሊሲ አውጪዎች በገበያ መሠረተ ልማቶችና መገልገያዎች ላይ መዋዕለ ንዋይን የማፍሰስን አስፈላጊነት እና ፋይዳ እየተረዱ መጥተዋል፡፡
- ከአርሶ አደሮች ጋር የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው በእንስሳት ገበያ ዉስጥ ሊኖሩ ከሚገባቸው አገልግሎቶች ዉስጥ የእንስሳት ህክምና ክሊኒኮች፣ የታጠሩ የገበያ ጥላዎች እና የውሃ ማጠጫ ገንዳዎች በቅደም ተከተል ተመራጭ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ለሙከራ የተሰሩ የገበያ ጥላዎች የአርሶ አደሮችን የበግ እና ፍየል ግብይት ተሳትፎ እና ከነዚሁ እንስሶች የሚያገኙትን ገቢ ጉልህ በሚባል ደረጃ ጨምሮታል፡፡

## መ ግ ቢ ያ

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚገኙ የእንስሳት ገበያዎች ብዙዉን ጊዜ በከተማ ወይም በአስተዳደር ማዕከላት ውስጥ ወይም ለነዚህ ቦታዎች ቀረብ ባሉ ስፍራዎች ላይ ይቆማሉ፡፡ እነዚህ ገበያዎች በአብዛኛው ግብይትን የሚያሳልጡ አገልግሎቶች ተቋማት አልባ ከመሆናቸውም በላይ ለእንስሶችም ሆነ ለከብቶቹ ባለቤቶች የሚመቹ አይደሉም፡፡

አብዛኛውን ጊዜ በገበያ ቀናት አርሶ አደሮቹ ለሰዓታት ከብቶቻቸውን እየነዱ በእግር መጓዝ ይኖርባቸዋል፡፡ በክረምት ወራት አርሶ አደሮቹ እና እንስሳቱ በመንገድ ላይ የሚገኙትን ወንዞች ተሻግረው ማለፍ ቢችሉ እንኳን ገበያ ከደረሱ በኋላ በዚያ መጠለያ ባለመኖሩ ብዙ ጊዜ በዝናብ ይደበደባሉ፡፡ በደረቅና ሞቃታማ ወቅት ደግሞ እንስሳቱ በፀሀይ ላይ ስለሚቆዩ በውሃ ጥም ከመሰቃየታቸውም በላይ አካላቸውም ሲጎሳቆል ይታያል፡፡ በዚህም ምክንያት በገጠር ያሉ የከብት ገበያዎች የሚቆሙት ለጥቂት ሰዓታት ብቻ ነው፡፡

በአጠቃላይ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ያሉ ደጋማ ቦታዎች የሚገኙ የእንስሳት ገበያዎች በቂ ያልሆነ መሠረተ ልማት እና ውስን ተደራሽነት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ የገበያ መሠረተ ልማቶች እጥረት አርሶ አደሮች በገበያ ውስጥ ከእርሻ ምርቶቻቸው የሚያገኙት ጥቅም እንዲቀንስ ከማድረጉም በላይ እነሱ እንደ ገዥ ከገበያ በሚገዟቸው የእርሻ ውጤቶች ላይ የዋጋ ጭማሪ ያስከትላል፡፡ በአጠቃላይ ከግብርና ምርቶች በተለይም ደግሞ ከእንስሳት የግብይት ስርዓት ጋር የተያያዙ

ILRI INTERNATIONAL LIVESTOCK RESEARCH INSTITUTE

ICARDA Science for resilient livelihoods in dry areas

ወጭዎች ከአርሶ አደሩ አቅም አኳያ በጣም ከፍተኛ ናቸው:: ይህም የሆነው የማጓጓዣ መገልገያዎች እጥረት አርሶ አደሮች እንስሳቱን እየነዱ ረዥም ርቀት በእግራቸው እንዲጓዙ ስለሚያስገድዳቸው ነው::

ከዚህ በተጨማሪ በገበያ ቦታዎች አካባቢ በመኖ አቅርቦት፣ በውሃ አቅርቦት፣ በከብቶች ሕክምና፣ በእንስሳት ማቆያ ቦታ፣ እና በገበያ መረጃ ዙሪያ ስር የሰደዱ ችግሮች አሉ:: አመቺ ባልሆኑ የገበያ ሁኔዎች ለከፍተኛ ምቾት ማጣትና ውጥረት የተጋለጡ እንስሳት ክብደታቸው ሊቀንስና የአካል ጉዳት ሊደርስባቸው እንዲሁም ሊታመሙ ይችላሉ:: የአገልግሎቶች በበቂ ደረጃ አለመኖር እና በዚህ የተነሳም ግብይቱ የሚካሄድው ባጭር ጊዜ ውስጥ በመሆኑ አርሶ አደሮቹ እንስሳቱን ገዢዎች ሊከፍሉ ከሚፈቅዱት ዋጋ በታች በሆነ ገንዘብ ይሸጣሉ:: ይሄም ሊያገኙ ይችሉት የነበረዉን ገቢ እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል::

ስለዚህ የገበያ መሠረተ ልማት እና መሰል በግብይቱ ስርዓት ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ታስበዉ የሚከናወኑ ተግባራት የእንስሳት እርባታውን ዘርፍ ለመለወጥ የሚደረጉ ጠቃሚ እርምጃዎች ናቸው:: የዘርፉ ማደግና መለወጥ ደግሞ ለድህነት ቅነሳ እና ለገጠሩ ነዋሪዎች የምግብ ዋስትና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል::

የእንስሳት እርባታው ዘርፍ ያለውን እና እስካሁን በጥቅም ላይ ያልዋለዉን አቅም ከግምት በማስገባት የኢትዮጵያ መንግስት የገበያ መሠረተ ልማቶችን በመገንባት የግብይት ሥርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ በቅርቡ አዳዲስ ጥረቶችን በማድረግ ላይ ነው:: እንደነዚህ አይነት ሥራዎች በገጠር የሚኖሩ እንስሳት አርቢዎች በሚያገኙት ጥቅም ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል:: በተጨማሪ ብዙ ገዥዎችና ሻጮች ወደ ገበያው እንዲመጡ ሊያደርግ እና የግብይት ወጭዎችን ሊቀንስ እንዲሁም ከእርሻ ምርቶች የሚገኘውን ትርፍ ሊጨምር ይችላል:: የገበያ መሠረተ ልማቶችን ማሻሻል የእንስሳት ግብይትን ብቃት ሊጨምርም ይችላል::

ይህ አጭር ጽሁፍ ባለፉት ስድስት ዓመታት ዉስጥ የተደረጉ እና ለእንስሳት ግብይት አገልግሎቶች ያለዉን የተጠቃሚዎች ፍላጎት እና ከነዚህ አገልግሎቶች አንዱ የሆነው የገበያ ጥላ ያስገኘውን ፋይዳ የሚያሳዩ ሳይንሳዊ ጥናቶችን ጭብጥ ያቀርባል::



Photo ICARDA/Girma Kassie

*የእንስሳት ገበያዎች ብዙውን ጊዜ የሚቆሙት የማይመቹ እና ለሌላ ጥቅም የማይዉሉ መሬቶች ላይ ነው::*



Choice Set 1
Card 1

| ገበያ 1 | ገበያ 2 | ይቅርብኝ |
|---|---|---|
| የገበያ ጥላ ያልታጠረ ጥላ አለው | የገበያ ጥላ ጥላ የለውም | |
| የእንስሳት ጤና ጣቢያ የለውም | የእንስሳት ጤና ጣቢያ አለው | |
| የማቆያ በረት የለውም | የማቆያ በረት አለው | |
| የዉሃ ገንዳ የለውም | የዉሃ ገንዳ የለውም | |
| ሽንት ቤት የሚፀዳ ሽ/ቤት አለው | ሽንት ቤት የለውም | |
| የመኖ መሸጫ አለው | የመኖ መሸጫ የለውም | |
| የአገልግሎት ክፍያ 12.50 ብር | የአገልግሎት ክፍያ 7.50 ብር | |

*ምናባዊ የበግና ፍየል ገበያዎች ማወዳደሪያ ካርድ*

## የጥናቱ ዓላማ እና ስልት

የዚህ ምርምር ዋና ትኩረት ገበያተኞች ለበግና ፍየል ገበያ አገልግሎቶች ያላቸውን ፍላጎት መጠን መለካት እና እነዚህ አገልግሎቶች በአርሶ አደሮች የገበያ ተሳትፎና ዉጤታማነት ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ መገምገም ነው:: ገበያተኞች ለገበያ አገልግሎቶቹ ያላቸው ፍላጎት የተለካው አገልግሎቶቹ በተለያየ ደረጃ እና ስብጥር የሚገኙባቸው ምናባዊ ገበያዎችን በማወዳደር ላይ የተመሰረተ ምርጫቸውን በማየት ነው::

የበግና ፍየል ገበያ ጥላ በአርሶ አደሮች የገበያ ተሳትፎ እና ዉጤታማነት ላይ ያመጣዉን ፋይዳ ለመለካት ደግሞ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ በእጣ በተመረጡ ዘጠኝ የበግና ፍየል ገበያዎች ሰርተናል:: የጥላዎቹን ፋይዳ ለመገመት ጥላዎቹ ከመሰራታቸው በፊት እና ተሰርተው ለሶስት ዓመት አገልግሎት ከሰጡ በኋላ በ 18 (9 የሙከራ እና 9 የማነጻጸሪያ) ገበያዎች ዙሪያ የሚገኙ ለናሙና በእጣ የተመረጡ ገበያተኞች ያሉበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሰፊ ይዘት ያለው መረጃ ተሰብስቧል::



*ከተሰሩት የገበያ ጥላዎች አንዱ*

## የተገኙ ዉጤቶችና ማስረጃዎች

አርሶ አደሮች ለበግና ፍየል ገበያ መገልገያዎች ትልቅ ፍላጎት አሳይተዋል። የእንስሳት ልማት ማሻሻያ ጥናት የሚደረግባቸው ቦታዎች ላይ የተገኘው ተጨባጭ መረጃ እንደሚያሳየው የእንስሳት ህክምና ክሊኒኮች፣ የታጠሩ የገበያ ጥላዎች እና የውሃ ማጠጫ ገንዳዎች በአርሶ አደሮች ዘንድ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው። በአንድ ጣቢያ በተለይ የተደረገ ጥናት ደግሞ የእንስሳት ማቆያ፣ የገበያተኛ መፀዳጃ ቤት፣ የእንስሳት ህክምና ክሊኒኮች፣ የውሃ ማጠጫ ገንዳዎች፣ የመኖ መሸጫዎች እና የገበያ ጥላዎች በአርሶ አደሮች የተመረጡ አገልግሎቶች እንደሆኑ አሳይቷል።

ከፍላጎት ጥናቱ በተጨማሪ የገበያ ጥላ በገበያ ተሳትፎ (ወደ ገበያ ከቀረቡ እንስሳት ቁጥር አኳያ) እና ስኬት (ከንስሳት ሽያጭ ከተገኘ ገቢ አኳያ) ላይ ያመጣዉን ለዉጥ ለመገምገም ተችሏል። የግምገማው ዉጤት እንደሚያሳየው የገበያ ጥላዎቹ አርሶ አደሩ ከበግና ፍየል የሚያገኘውን ገቢ በ40% ጨምሮታል። በተመሳሳይ የገበያ ጥላዎቹ የአርሶ አደሩን የገበያ ተሳትፎ በጉልህ አሻሽለዉታል። አርሶ አደሮቹም ይህን ለውጥ በደስታ ተቀብለውታል። ጥላዎቹ በመገንባታቸው ምክንያት አርሶ አደሮቹም ሆነ እንስሳቱ በግብይት ወቅት በዝናብና በፀሀይ አይቸገሩም። በዚህም ምከንያት አርሶ አደሮቹ እንስሶቻቸውን ገዢዎች ሊከፍሉ ከሚፈቅዱት በታች በሆነ ዋጋ በቶሎ ለመሸጥ ስለማይገደዱ ከሽያጩ የሚያገኙት ጥቅም ጨምሯል።

## ለስኬቱ ምክንያቶችና አስተዋጽኦ ያደረጉ ጉዳዮች

ከላይ የተጠቀሱት የገበያ አገልግሎቶች አዎንታዊ የሆነ ለውጥ ያስከተሉበት ምክንያት በበግና ፍየል ግብይት ስርዓት ዉስጥ ያለውን ወሳኝ ክፍተት መሙላት በመቻላቸው ነው። በጥንቃቄ የተነደፉና በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የእንስሳት ግብይቶችን ለማሻሻል የሚሰሩ ሥራዎች በእርግጥም በጣም ጠቃሚ ናቸው። ነገር ግን የተለያዩ ተሳታፊ አካላት በገበያ አገልግሎቶች ላይ መዋዕለ-ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ለማበረታታት ብዙ ቅድመ ሁኔታዎች መልስ ማግኘት ይኖርባቸዋል። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- የኢትዮጵያ መንግስት የግሉን ዘርፍ በማብቃት እና በእንስሳት ገበያ ልማት ላይ ግልጽ የሆኑ መመሪያዎችን በማዉጣት ዙሪያ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል።
- የገበያ አገልግሎቶችን የማልማት ስራ ከመንገድ አውታሮች ግንባት ጋር የተጣመረ እንዲሆን መንግስት እና የአካባቢው ማህበረሰቦች መስራት አለባቸው።
- የመሬት ባለቤትነትን ጉዳይ እንደገና በመገምገም በየደረጃዉ ያሉ የመንግስት ባለስልጣናት የእንስሳት ገበያዎችን የሚያበረታቱ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ማስቻል ያስፈልጋል።

## የተገኘው ትምህርትና ለማስፋፋት መታሰብ ያለባቸው ጉዳዮች

**የገበያ አገልግሎቶች** አርሶ አደሮችን እና እንስሳትን ከአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ፣ ከውሃ ጥም እና ከሌሎች ችግሮች ይታደጋሉ:: አገልግሎቱ አርሶ አደሮቹ በገበያው ረዘም ላለ ጊዜ እንዲቆዩ ከማድረጉም በላይ እንስሳቱ ላይ የሚደርሰውን እንግልት ይቀንሰዋል:: ይህ መሆኑ ደግሞ የአርሶ አደሩን የመደራደር አቅም ይጨምረዋል::

**የበግ እና ፍየል ገበያ ጥላ** አርሶ አደሮች ከፍተኛ ዋጋ ከሚሰጧቸው መገልገያዎቹ አንዱ ነው:: ጥላዎቹ ገበያተኞችን እና እንስሳቱን በበጋ ከሚየቃጥል ፀሐይ  እና በክረምት ደግሞ ከዝናብ እንደሚጠብቃቸው ይገነዘባሉ:: አሁን ባለው ሁኔታ ከባድ የፀሐይ ሙቀት እና ከፍተኛ ዝናብ አነስተኛ አቅም ያላቸው አርሶ አደሮች ገበያ ዉስጥ ብዙ ጊዜ እንዳይቆዩ እና እንስሳቱን ባልጠበቁት ዝቅተኛ ዋጋ እንዲሸጡ እያስገደዳቸው ነው:: በፀሐይ ሙቀት እና በከፍተኛ ቅዝቃዜ ምክንያት የሚመጣ መጎሳቆል እንስሳቱን የተዳከሙና የታመሙ በማስመሰል ሊያወጡ የሚችሉትን ዋጋ ይቀንሰዋል::

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ውስጥ በተጨባጭ የታየዉ **የገበያ ጥላዎች ሚና** የእንስሳት ገበያ መገልገያዎችን ለማስፋፋት እንደ ጠቃሚ መነሻ ሊጠቅም ይችላል:: ምንም እንኳ ለተለያዩ መገልገያዎች የሚሰጠው ክብደት ከአካባቢ አካባቢ የሚለያይ ቢሆንም የእንስሳት ገበያን ለማሳደግ የሚደረጉ ሥራዎች ለማቆያ በረት፣ ለገበያ ጥላዎች፣ ለመፀዳጃ ቤቶች፣ ለእንስሳት ህክምና አገልግሎቶች፣ ለውሃ  ማጠጫ ገንዳዎች እና ለመኖ መሸጫ መደብሮች ቅድሚያ የሰጡ መሆን አለባቸዉ::



Photo ILRI/Zerihun Sewunet

አንዲት በግ ገዢ በግ ስትመርጥ

## ምስጋና

ይህ ምርምር፣ ዓለምአቀፍ የግብርና ምርምር አማካሪ ቡድን (CGIAR)፣ በእርባታ እንስሳት ላይ በሚያካሂደው የምርምር መርሃ-ግብር ውስጥ ሲደረግ ቆይቶ፣ በCGIAR ዘላቂ የእንስሳት ምርታማነት ኢኒሼቲቭ ውስጥም ቀጥሏል:: የCGIAR ምርምር የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ከCGIAR Trust Fund አስተዋፅዖዎች ነው:: CGIAR የምግብ ደህንነቱ የተረጋገጠበት መጪ ዘመን እንዲፈጠር የሚሠራ ሉላዊ የምርምር ሕብረት ሲሆን፣ በአየር ሁኔታ ቀውስ ውስጥ የምግብን፣ የመሬትን፣ እና የውሃን ሥርዓቶች ለማሻሻል በቁርጠኛነት ይተጋል:: በተጨማሪም፣ እነዚህ የምርምር ወረቀቶች ወደአማርኛ እንዲተረጎሙ እና የገፅ ንድፋቸው እንዲሠራ፣ የCGIAR የአየር ሁኔታ ምርምርን ተፅዕኖ ማቀለጠፍ ለአፍሪካ (AICCRA) ለተሰኘው ፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፍ ላደረገው የዎርልድ ባንክ አካል ለሆነው ዓለም-አቀፍ ልማት ማኅበርም (IDA) ምስጋና እናቀርባለን::

## አጋሮች

ስማርት ኢትዮጵያ ፕሮጀክት ከዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ተቋም (ILRI) እንዲሁም እንዲሁም ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር እንስቲትዩት  (NARS) ጋር በመተባበር በዓለም አቀፍ የቆላ አካባቢ ምርምር ማዕከል (ICARDA) የሚመራ ነው::

### ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት

ዶ/ር ግርማ ተስፋሁን g.tesfahun@cgiar.org

ይህን ህትመት ለመጠቀም ፍቃድ የሚሰጠው the Creative Commons Attribution 40 በተባለ ዓለም አቀፍ ፈቃድ ሰጭ በኩል ነው:: ኦክቶበር 2021